# ኖርዌይ ሲገቡ የሚደረግ የሳምባ ምች (TB) በሽታ ምርመራ

ሁሉም ወደ ኖርዌይ የሚመጣ ሰው፣ ጥገኝነት ፈላጊም ሆነ ስደተኛ፣ የሳምባ ምች (ቲቢ) ምርመራ ማድረግ አለበት። የሳምባ ምች ከተስፋፋባቸው ሀገሮች የመጡ ሌሎች ስደተኞችምምርመራው ያስፈልጋቸዋል። ምርመራው ያሳምባ (ደረት) ራጅ እና የደም ወይም የቆዳ ምርመራን ያካትታል።

## የደረት ራጅ

የደረት ራጅ የሚወሰደው ጥቂት ደቂቃዎችን ብቻ ሲሆን እርስዎን አይጎዳም። የደረት ራጅ መነሳት ነፍሰጡር ቢሆኑም እንኳ የደህንነት ስጋት የለውም። ጥሩ የራጅ ምስል ለማግኘት፣ ከወገብ በላይ ልብስዎን ሁሉ ቢያወልቁ መልካም ይሆናል። ከፈለጉ፣ ቁልፍ ወይም ጌጣጌጥ የሌለው ስስ ካናቴራ ሊለብሱ ይችላሉ። የጡት ማስያዣዎችዎም መውለቅ አለባቸው። ራጁ በሚወሰድበት ጊዜ ትንፋሽዎን ወደውስጥ ስበው መያዝ አለብዎ።



አንዳንድ ሰዎች የደም ወይም የቆዳ ምርመራ ማድረግም ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

**የደም ምርመራ (IGRA):-**



**የቆዳ ምርመራ (Mantoux):-**



የምርመራውን ውጤት ወዲያውኑ አይደርስም። የተወሰኑ ቀናት ይወስዳል። ምርመራዎቹ  ሌላ ተጨማሪ ምርመራ እንደሚያስፈልግዎ ወይም ከዶክተር ጋር መነጋገር እንዳለብዎ ሊያመለክቱ ይችላሉ። ያን ጊዜ እናገኝዎታለን። ይህ ማለት ግን የሳምባ ምች (የቲቢ) በሽታ ተጠቂ ነዎት ማለት ላይሆን ይችላል።

የቲቢ በሽታ ምልክቶች የሚያካትቷቸው ለብዙ ጊዜ (ለሶስት ሳምንት ወይም ከዚያ በላይ) የቆየ ሳል፣ ትኩሳት፣ የክብደት መቀነስ፣ የድካም ስሜት፣ ሌሊት ሌሊት ማላብ ወይም በአንገት ውስጥ ፣ በጭን ውስጥ ወይም በብብት ስር የሚፈጠሩ እባጮች ናቸው። የሳምባ ምች ባክቴሪያ በሰውነትዎ ውስጥ ኖሮ ነገር ግን የሳምባ ምች በሽታ ተጠቂ ላይሆኑ ይችላሉ። ያልታከመ እና በሳምባ ውስጥ ያለ ቲቢ (ፐሉሞናሪ ቲቢ) ብቻ ነው ወደ ሌሎች ሊተላለፍ የሚችለው።

ቲቢ ካለብዎ በኖርዌይ ውስጥ በነፃ ህክምና ያገኛሉ። ከዚህም በላይ ህክምናዎን እስኪጨርሱ በኖርዌይ ውስጥ የመቆየት መብት ይሰጥዎታል።

ቲቢ የሚድን በሽታ እንደሆነ ያስታውሱ! ለተጨማሪ መረጃ ይህንን ድረገፅ ይጎብኙ:- www.fhi.no

Norwegian Institute of Public Health